# ሁላችንም አማሮች ካልሆን ኢትዮጵያ አትድንም

ይነጋል በላቸው

እንደዚህ ዓይነት ርዕስ እንኳን አንባቢን ጸሐፊንም ያስደነግጣል። በተለይ በዚህ ሁሉም ነገር በተወነዠባበረበት የኢትዮጵያ ምድር ‹አማራ ሁን› ብሎ መስበክ ምን ያህል ቂልነት እንደሆነ ማንም አያጣውም። ‹ካንተም አልበጀ ልጄ› ነበር ያሉት? እኚያ በልጃቸው መቃብር ዘንድ ጧት ጧት እየተገኙ ‹ጥራኝ ልጄ፤ ጥራኝ ልጄ› በማለት ዘወትር ያለቅሱ የነበሩ ሴት - አንዱ የልጃቸው ጓደኛ በመቃብሩ ሥር ተደብቆ ስማቸውን ከተጣራ በኋላ ‹ነይ እማዬ› ባላቸው ወቅት? አዎ! ለነሱም - ለአማሮቹም ባልበጀ ዘመን ‹አማራ ሁኑ› ብሎ በግልጽ ማወጅ አንድም የለየለት ዕብደት ነው፤ አንድም እንደአንዳንዶች ታሳቢ የአጸፋ መልስ ‹ድንቁርና› ነው፤ አንድም ‹ትምክሕት›ና ‹ዕብሪት› ነው፤ አንድም ለሀገር ትንሣኤ ከመጨነቅ የመነጨ ሊካድም የማይገባው እውነት ነው። በፈለጋችሁት ተርጉሙት - ለሀገራችን ምስቅልቅል ችግሮች ዋነኛ መፍትሔው ዕቅጩን ዕወቁት አማራ መሆን ነው። ሌሎች ሰዎች በተዘዋዋሪ ካልሆነ በቀጥታና በግልጽ ይህን መሰል አቋም ሲያንጸባርቁ ሰምቼ አላውቅም - አማራነት ለኢትዮጵያዊ ስብዕና ትንሣኤ ዋና አብነት ስለመሆኑ።

አሁንም ሌላ ሥጋቴን ልግለጽ። የምለውን ለመረዳት ትዕግስትና አስተዋይነት ይጠይቃል። ወደምለው መሄዳችን ካይቀር በችኩልነት በስሜት ከመቆጣት ተቆጥበን ይህችን አጭር ሀተታ በንባብ እንዝለቃት። ከዚያም አንዳችን እሚጎድለንን ሌላኛችን እሚልተን ወደጋራ መግባባት እንምጣ። እሚያዋጣን ያና ያ ብቻ ስለሆነ። የዛሬን ትርምስምስ ተውት፤ በብዙ ቦታዎች እሚታየው ነገር በህልምና በቅዠት የተቃኘ በዱባ ጥጋብ መዘውርም እሚሽከረከር የዘመን ወጀብ ነው - ያልፋል፤ ሌሎች ነውጦችና የዕልቂት አዝመራዎች እንዳለፉ ሁሉ ይህም ነጎድጓድ ዕድሜውን ጨርሶ ወደታሪክ ጎተራ ይከተታል። ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም ብሏል ጠቢቡ ሶሎሞን። ይህ ዘመን እንዳልነበር ሁሉ ያልነበር ዘመንም ይብታል - ሊያውም በቅርብ። የመጨካከሙ መንስኤ የሌሊቱ መንጋት ምልክት መሆኑን መጠራጠር አይገባም። ሚሽሾ በጠወለገና በጨለመ ተስፋ ውስጥ የሚረገዝ አዲስ የተስፋ ብርሃን ሲወለድ ‹ልጁን አንሽ ምጡን እርሺ› የሚያሰኝ ይሆናል። ...

> ከዚህ በላይ ያለው ሃሳብ በዚያን ሰሞን ጀምሬ የተውኩት ነበር። አሁንና ሰሞኑን ደግሞ የአማሮች በወያኔው ‹ነጻ አውጪ› ጉጅሌ ከመኖሪያ ቦታ መፈናቀልና መሰቃየትን በሚመለከት የወቅቱ ዜናና ሀተታ በመሆኑ የጀመርኩትን መጣጥፍ መቀጠልን ወደደሁ። በዚያ ላይ እጅግ በምወደውና በማከብራው እንደ አንድ የኢትዮጵያ ተስፋ አድርጌም አንጋጥጬ የማየው ኦባንግ ኦ. ሜቶ በንቅናቄው ስም ያወጣው የአማሮችን የሀገር ውስጥ ስደትና እንግልት የተመለከተ መግለጫ ሳነብ ስሜቴ ተነካ። እናም የጀመርኩትን ጦማር ቀጠልኩ። በታሪክ ጉግል ይጎለጎል ዘንድ።

አኢጋን ባወጣው ዘገባ 78 ሺህ አማሮች ለዓመታት ከኖሩባቸው ሥፍራዎች አንድም ሀብትና ንብረት ሳይዙ በወያኔው አጀንዳ አስፈጻሚዎች እየተባረሩና ለመከራና ሰቆቃ እየተጋለጡ እንደሆነ ተረድተናል - ቢያንስ ተረዳን - በ‹ተረዳን› ቃል ሁለንተናዊ ትርጓሜው፤ የመርዶ እንጂ የብሥራት ዜናማ ከየት መጥቶ? ያሳዝናል፤ ያስቆጫል፤ ግን እንደአማራነት አይደለም ሊያስቆጭ እሚገባ። እንደሰው እንጂ፤ ሰው ክቡር ፍጡር ነው። ከሁሉም በፊት ዘርና ዘር ማንዘር ሳይሆን ሰው ነው ሊታወሰን እሚገባ። አለበለዚያ የሦርያውያን ሞትና ስቃይ፣ የኢራቃውያን የዕለት ተለት ፍናዳታና ዕልቂት፣ የፍልስጥኤማውያንና እስራኤላውያን የሰቆቃና የሥጋት ሕይወት፣ ... አይሰማንም ማለት ነው። ሰው ስንሆን ነው አእምሮአችን ሰፋ ባለ ሁኔታ ዓለምን እሚገነዘበው። በሀገራችን - የጋራ በምንላት የወያኔ ‹ኢፌድሪ› (ኢሕድሪ ይሻለኝ ነበር ልበል?) - ሰው ሰው መሆኑን ረስቶ - ከለየለት የአውሬነት ደረጃም እጅግ ወርዶ ወገኖቹና ወንድም እህቶቹ መሆናቸውን በመገንዘብ በመንፈስም በሥጋም ይበልጥ እንዲያድጉና እንዲፋፉ ማገዝና መተባበር ሲገባው ይህን የመሰለ ውርጅብኝ ማድረስ በምንም መለኪያ ሲመዘን ሰው ነኝ ብሎ እሚያምንን ፍጡር ያስደነግጣል፤ ከዚህ ዘግናኝ ሀገራዊ እውነታ በመነሣት መዳረሻችንንም ስናስበው ከፉኛ ያስጨንቃል። የዛሬ ሃያና ሠላሳ ዓመታት ይሁነኝ ተብሎ የተያዘ ዘርን የማጥፋት ወያኔያዊ ተልዕኮ የዘመናት መለዋወጥና የወቅቶች መፈራረቅ አንዳችም አወንታዊ ተጽዕኖ ሳያደርጉበት እንዲህ በጥፋት ማዕበል እየጎመራ መምጣቱ የሰውን ልጅ ምን ነካው በሚያስብል ራስ ምታት እሚለቅ ጥያቄ አእምሮን ያናውጣል። በዚህ የሞተ ጉዳይ ይብቃኝ መሰል።

ሁላችንም አማራ እንሁን። ብዙዎቻችን ለጊዜው ሰው መሆን ሊያቅተን ይችላል። በኢትዮጵያ ምድር ቢያንስ የዕለት ጉርስና የዓመት ልብስ ኖሮን በሰውነታችን ተከብረን እንድንኖር ከፈለግን በአዲስ መልክ አማሮች መሆን ይኖርብናል። ከዚያ በኋላ ነው ወደሰው መሆን የተሚላ ደረጃ መሸጋገር እሚቻለን። ሰው መሆን - ወንድሞችና እህቶች - ከባድ ትግል ነው፤ የፍጹም ሰው ማንነት መገለጫዎችን ፈላልጋችሁ አንብቡና ራሳችሁን መዝኑት። ብዙዎቻችን ገና እንስሳት ዓለም ውስጥ ነው እምንገኝ - ኧረ ለዚህም የታደሉ ጥቂቶች ናቸው! ብዙ እንስሳት እኮ ርስ በርስ አይባሉም። እኛ እኮ እየተባላን ነው። ሥጋችንን እንዳይመስላችሁ። (የምሥራች፡- ለፋሲካ ዶሮ 300 ብር ገባ፣ ኪሎ ቅቤ 250 ገባ፣ ጤፍ 1800 ብር ገባ፣ ሌላውም እንዲሁ። ከዚህ በላይ የዐውዳመት ምሥራች የለም። ደስ ይበለን፤ ሃሤትም እናድርግ።)

ለመሆኑ አማራ ማን ነው?

አማራ ማለት ብዙ ነገር ማለት ነው። ክቡር ክፍሌ ወዳጆም አማራ ነው ወይም ነበር። ክብርት ገነት ዘውዴም አማራ ናት - እሷም ዕድር ስለሌላት ቀባሪ ጠፍቶ እንጂ ሙት ነችና ‹ነበረች› ልበላት። ክቡር ዳዊት ዮሐንስና አሰፋ ብሩም አማራ እንደሆኑ ይነገራል - አሁን ምን እንደዋጣቸው ባይታወቅም። ልዑል ሙሉጌታ ለሥራተ ካሣም አማራ ነው አሉ። ሌላ ‹ትልቅ› አማራ መጥራት ሊያቅተኝ ነው እንዴ እናንተዬ? አዎ፣ እነኚህንና ሌሎቹን አማሮች የመሳሰሉ ከርሳም አማሮች ሞልተዋል። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው። የትግሬ አማራ እንዳለን ሁሉ የአማራ ትግሬም አለ። የአማራ ኦሮሞ እንዳለን

EthioLion.com

ሁሉ የኦሮሞ ትግሬና አማራም አለን። የጉራጌ ትግሬ እንዳለ ሁሉ የትግሬ ጉራጌና የሶማሌ አማራም አለ። አማራን ከሚያጠፋ በስም ‹ሀ› ከሚባል ኃይል ጎን ተሰልፎ ‹ዘራፍ አማራን ገዳይ!› የሚል አጋሰስ አማራ እንዳለ ሁሉ በተቃራኒው አማራንና ሌሎች ምሥኪን ኢትዮጵያውያንን ለማጥፋት ከተሰለፈውና ከዚሁ በስም ‹ሀ› ተብሎ ከተጠቀሰው ወገን በዘሩ እሚመደብ ሆኖ ሳለ በተስተካከለ ፍትሃዊ ዓላማ ላይ በመቆሙ ግና ለአማሮች ትድግና ሕይወቱን እስከመሰዋት እሚደርስ ቅንና የማተቡ ሰው አለ። ነገሩ ሁሉ የተዘበራረቀና የተወሳሰበ ነው። በዕንቆቅልሽ ምን አውቅልሽ ዓይነት የታሪክ ድርና ማግ ውሉን የሳተበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን - ሊያልፍ ያከፋናል አባካችሁን።

አማራ እንደመንግሥቱ ኃ/ማርያም የብካኔ ይሁን ጥናታዊ ፍቺ በተራራ ላይ እሚኖር ሕዝብ ማለትም ይቻላል - ግን በተራራ ላይ እማይኖር ማን አለ ዳሩ? ችግሩ የመኖሪያው ጉዳይ አይደለም ወንድሞችና እህቶች። ችግሩ የመልክና ቁመት የቋንቋና ሃይማኖትም አይደለም። ጥያቄው የአመለካከት ነው - የአስተሳሰብ።

ትልቅ መጽሐፍ እሚያጽፍ ነገር እኮ ነው እየዳከርኩበት ያለሁት። አኢጋን እንዳለው የአማራ ደም ምን ዓይነት ይሆን? ጥቁር ይሆን ቅጠልያ? ነጭ ይሆን ሰማያዊ? አማራ ማለት ግን ምን ዓይነት ‹ግርማ ሞገስ› ያለው ፍጡር ይሆን ጎበዝ? ስሙን ብቻ ማለቱ ነው። **አማራ!** ወያኔን ሌት ከቀን እንዲህ እሚያስቃዥና እሚያስባንን ዕንቅልፍም እሚነሳ አንዳች መስተደንግጻዊ ድግምት ያለበት ስም መሆን አለበት። እንደራስ ሆቴሉ አንበሣ ከሞተም በኋላ የማስደንገጥ ኃይሉ ያልበረደ ምትሃታዊ ፍጡር ፤ አማራ። ‹ምነው አማራ በሆንኩ!› እሚያስብል የሚያስቀና ፍጡር። እኔ በበኩሌ ቀናሁበት፤ ‹በሆንኩኝ›ም አልኩ። መሞከሬ አይቀርም - ከተሳካልኝ።

እናስ ሁላችን አማራ ብንሆን ምን ያሳፍራል ጎበዝ? ምንም።

ጨዋታ በወዝ ሲቀባ ጥሩ ነው። ፈገግ እያሉ እሚያነቡት ነገር ከአእምሮ በቶሎ አይጠፋም - መጥፋቱ ባይቀርም።

የምር ጨዋታ። አማራ ሆዱ እንጂ ሌላ ጠላት የለውም - የአሁኑን አያድርገውና ብሎ ምርቃት ቢጤ ጣል ማድረግም ይቻላል ለዚህ ዐረፍተ ነገር። አማራ ወንዘኝነትና አልፍ ሲልም የዘመድ አዝማድና የጎጥ ጉዳይ እንጂ ዘረኝነት አያጠቃውም - እኔ እማውቀው የዱሮ አማራ። ዘመድ አዝማድ ሲባልም አጥንትን እንደውሻ እያነፈነፈ ሳይሆን (አልፎ አልፎ እንደወረት ሊቆጠር በሚችል ሁኔታ ይህ ዓይነቱ ብልግና እውን ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩ በታሳቢነት ተይዞልኝ) የማንም ዘር ሆኖ ነገር ግን ይበልጥ ለሚቀርበው - ከእናቱ ልጅም አስቀድሞና አስብልጦም ለሚወደው ሊያደላ እንደሚችል ዐውቃለሁ። አማራ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ እንጂ በተበጣጠሰና በከሃዲዎች ቤተ ሙከራ ውስጥ ተበጅቶ በሚሰጥ ባንዲራ አያምንም። አማራ ለአንድ ሉዓላዊ ሀገርና ለአንድ ሕዝብ ሀገራዊ ኅልውና አነጣጥሮ ያልማል እንጂ በቋንቋና በዘር ለተዋቀረ ከፋፋይና መሠሪ ዓላማ ተሸንፎ አያውቅም። አማራ የእኔ የሚለው ሌላ የማንነት መገለጫ የለውም - ከኢትዮጵያዊነት በስተቀር። አማራ አማርኛ ሲነገር ቢሰማ ልቡ በዘውጋዊ ጠባብ መግነጢሳዊ ኃይል ተማርኮ መንፈሱ ወደጎጃምና ጎንደር ወይም ወሎና ገጠራማው ሸዋ ወደሸንኮራና ቅምብቢት አይሸፍትም። አማራ ከአንዲት ኢትዮጵያ በስተቀር የሚመካበትም ሆነ የሚኮራበት የራሴ የብቻየ የሚለው ሃይማኖታዊም ሆነ ዘውጋዊ የመሰባሰቢያ የጽዋ ማኅበር የለውም። አማራ በዘረኝነት ልክፍት ተመርዞ የመንግሥት ተቋማትን ሙሉ በሙሉ በራሱ ሰዎች አይቆጣጠርም። ይህን መሰሉን ተንኮል አማራ ቢያውቅ ኖሮ ወያኔ አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት አይደለም ከደደቢት በረሃም ሊወጣ ባልቻለ ነበር፤ አማራም ሆነ ኦሮሞ በዚህ ረገድ ሞኞች ነበሩ፤ ናቸውም። ያምናሉ ግን ያመኑት ይከዳቸዋል እንጂ እነሱ ባሉበት አሉ (ባሕርያቸውን ለመግለጥ እንጂ ነገድን ከነገድ ለመለያየት አስቤ እንዳልሆነ አባካችሁን ተረዱልኝ)። ሌሎች ጠባብ አስተሳሰብ አላቸው ለማለት እንዳላሰብኩ ይታወቅልኝና አማራ ቢያንስ በአማራነት ከፍ ያለ የኅልውና ደረጃው የጠባብነት አስተሳሰብ ሳይሆን የሰፊ አስተሳሰብ ባለቤት ነው - ይህ አስተሳሰቡ እንደጎዳው ቢታወቅም ዕድገቱና ከአካባቢው ያገኘው ግንዛቤ ይሄውና ይሄው ብቻ ስለሆነ ከእንግዲህ ወደታች ወርዶ ወንዘኛና ሸረርተኛ አይሆንም፤ ወደ በቆረበው ሰፊ አመለካከቱ ይሞታታል ብዬ አምናለሁ። ይህ ጠባዩ ባፈራበት ተባይ ምክንያት ለማያባራ ሰቆቃና መከራ ከመጋለጡ በስተቀር አማራ ‹ጠላቱ እነዚህ ናቸው፤እነሱን ካላጠፋሁ እንቅልፍ እሚባል ባይኔ አይዞርም› ብሎ ምሎ ተገዝቶ በማንም ላይ ጦር ሰብቆ አያውቅም፤ ወደፊትም ጦር ቀርቶ ማማሰያ አይሰብቅም።...

እርግጥ ነው - ከስንዴ መሃል እንክርዳድ ፣ ከገብስ መሃል ወሸከሬ፣ ከጨዋ መሃል ባለጌ አይጠፋም። የአማራነት መልካም ገጽታ ውስጡን ያልዘለቀው፣ የምንደኛ ጠላቶቹ የፕሮፓጋንዳና የፍርፋሪ ጥቅም ሰለባ የሆነ፣ በፊቱ ያለው ሆዱ በጀርባው ዞሮ እያዳፋ ወደመታረጃ ቄራ እሚወስደው፣ በአማራነት የአጋጣሚ ፍጥረትነቱ በከንቱ እሚኮፈስና ቢከፍቱ ተልባ የሆነ፣ ወቅት እየጠበቀ ማንነቱን እንደእስስት እሚለዋውጥ ዓሣማና ጅብ አማራ በሀገር ውስጥም በውጭውም የለም ማለት እንዳልሆነ ሊታወስ ይገባል። አሁን ለተነሳሁበት ዓላማ አይጠቅምም እንጂ ስንትና ስንት የቆሸሸ ሰብዕና ያላቸው ማፈሪያ አማሮችን እየዘረጠጥኩ ለታሪክ ‹litter bin› (የቆሻሻ ማጠራቀሚያ) በዳረግኋቸው ነበር። ምን አስቸኮለኝ - ይደርሳል። ...

ቀደም ስል የተናገርኩት ቃል አለ፤ ችግራችን የዘርና ጎሣ ሳይሆን የአመለካከት ስለመሆኑ። እንደ እውነቱ አሁንም ቢሆን የአመለካከትና የጥቅም ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አማራና ትግሬ በምንድን ነው እሚለየው? የፊት ላይ ምልክቶቹ እንደሆኑ መስቀሉም ይሁን 11 እና 111 ቁጥሮቹ ሃይማኖታዊ ትዕምርቶችና ባህላዊ የጤንነት መጠበቂያ ዘዴዎች እንጂ ዘርን አይጠቅሱም፤ ለማንም ያልተከለከሉ ወይም በሕግ ያልተፈቀዱ ልማዳዊ ክንዉኖች ከመሆን አልፈው የማንነት ማጠየቂያ ሊሆኑ አይገባቸውም። ትግራይ ውስጥ የተወለደ አማራ 11 ቁጥር ታርጋ ቢለጥፍ ትግሬ ነው ማለት ይቻላል? እርግጥ ነው በኔ ሥሌት ትግሬ እንጂ አማራም ሆነ ሌላ ሊሆን አይችልም። ለምን - ትግሬነትም ሆነ አማራነት በትውልድ ሐረግ ሳይሆን

EthioLion.com

በአካባቢው በባህሉና በቋንቋው እየተመላለሱ ማደግን ስለሚጠይቅ። ከአማራ ቤተሰብ ተገኝቶ ሙልጭ ያለ ቻይናዊ ቢሆን ሊገርመንና በዚህ ሰው ማንነትም ጣልቃ እየገባን ልናስቃየው አይገባም። የማንነት ጥያቄ የትልቶች ችግር ነው። ሕጻናት ዘንድ ይሄ ችግር የለም፤ ለዚህም ነው ክርስቶስ ሕጻናት ካልሆንን መንግሥቱን መውረስ እንደማንችል የሚያሳስበን። ንፍጥ ከደረቀ በኋላ ትምህርትና ማንነት ያንገላታሉ። አይገቡንም - ግን ያሰቃዩናል። የማኅበረሰቡ ተፅዕኖም እንደዚሁ ቀላል አይደለም። እንጂ ሁሉም የአዳምና የሔዋን ዘር ነው። ዛሬ ተደርሶ መልክ ነጣ ጠቆረና - ፀጉር ዞማና ኪንኪ ሆነና - ሀብትና ንብረት መጣና- ክሳትና ውፍረት ግምት ውስጥ ገባና - ወይጦና ሺናሻ መባል ተጀመረና መነሻ ታሪክን ይለውጣል ማለት አይደለም።

ከፍ ሲል ስለአማራ የጠቃቀስኳቸው ነገሮች በቀጥታ ከአመለካከት ጋር እሚገናኙ ናቸው፤ ስለደም ‹ጥራት›፣ ስለአጥንት ‹ንጽሕና›፣ ስለዘር ማንዘር የትውልድ ሐረግ… በጥልቀት አላነሳንም። ያ ሰው ሠራሽ ሰዎችን የመከፋፈያ መንገድ ነው። እናም በመሠረቱ ይቅላም ይጥቆርም፣ ይንጣም ይወይብም የሰው ዘር አንድና አንድ ነው - በላይኛው አንቀጽ እንዳየነው። አንድ ፍጡር ከአንድ ፍጡር በሥነ ፍጥረታዊ እሳቤ ይለያል እሚባለው የአንዱ ደም ወይም ሌላ የሰውነት ክፍል ከሌላው አልገጥም ሲል ብቻ ነው። ዓይነቱ እስካልገደበን ድረስ የኔ ደም ለመለስ ዜናዊ አይሆንም አይባልም።የኔ ጣፊያ ለቢል ክሊንተን ወይም ለኦባማ አይገጥምም አንልም። የኔ ጉበት - አይ ይቺስ ትቅርበት - አልቃለች - የኔ መቅኒ ለመራራ ጉዲና አይሆንም አንልም። ያንተ የወንድሜ ኩላሊት ለሁንግ ቻንግ አይሆንም ብንል ስህተት ነው - ልክክ ብሎ ይገጥማል፤ ሰዎች ናችሁና። ስለዚህ ሁላችንም የሰው ዘሮች ነን፤ በመልክና በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በመልክዓ ምድር፣ በዖታና በመሳሰለው መለስተኛና አንዳንዴም ጠቃሚ ልዩነት ቢኖረንም ያ ዓይነቱ ተፈጥሯዊ ልዩነት ግዘፍ ነስቶ እንዲህ አንዱ የማኅበረሰብ ክፍል (እንወክለዋለን በሚሉ ሕገ ወጥና ወጥ ረገጥ ልጆች አማካይነት) ጦር ሰብቆ ሌላውን እስኪያጠፋ ድረስ ሊያስኬደን አይገባም። የተወሰኑት ቢያጠፉና ሲያጠፉም ‹ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ› ይባላልና ሃይ ማለቱ ባልከፋ ነበር። ይሁን ንግርቱ ይሠምር ዘንድ ሰለሆነ ከእስካሁኑ ከእስካሁኑ በላይ አንቆጭ። ስለወደፊቱ ግን ከላይ ወይም ከጎንና ከታች ብቻ አንጠብቅ። እኛም የምንጫወተው ሚና ይኑረን። ዝም አንበል። አንዶድም ውኃ የወሰዳት በሞኘነቷ ነው።

የዘር ሐረግ ወይም የዘውገኝነት ጣጣ ባለበት ይቀመጥ። ዱሮ የነበሩ ችግሮች ይታከሙ። ‹ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን› ተባብለን የ‹እንዲህ ነበርክ› ‹እንዲህ ነበራችሁ› ታሪክ እያነሱ መናቆር ይቅር፤ በፍጹም አንድ ኢንች አንዲት ጋት ወይ ስንዝር አላስኬደንም - አያስኬደንምም። እንዲሁ ዝም ብለን ብቻ አማራ እንሁን። ብዙ አማራ ያልሆኑ አማሮችም እንዳሉ እንረዳ። ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ በቅርቡ በአማራነት ጠበል ተጠምቀዋል። እናም አማራ ሆነዋል። ወንጀል አይደለም። ኃጢያትም አይደለም፤ ኦሮሞነቱን ማን ይወስድባቸዋል? ሁላችንስ ኦሮሞ አይደለንም እንዴ? ዕድሜ ለ16ኛው ክፍለ ዘመን የኦሮሞ - ምንድን ነው እሚባለው - እንቅስቃሴ - ኦሮሞ ያልተቀላቀለበት ኢትዮጵያዊ ሥፍራ አለ ለመሆኑ? ‹ንጹሕ እንዲህ ያለ ነገድ ነኝ› ብሎ እሚመጻደቅ ሰው የመጨረሻው ውሸታምና ለሀገር መፈራረስ ትልቁ ነቀርሣ ነው - ይቺን ዐረፍተ ነገር ደግማችሁ ተመልከቱልኝማ። እናም አማራ መሆን ማለት ማንነትን መካድ አይደለም - አስተሳሰቡ ነው ዋናው ተባብለን የለም ከላይ? ዶክተር መረራም አማራ ሆንዋል። ዶክተር ብርሃኑ ነጋም አማራ ነው - ሌላ ሆኖ እሚያውቅም አይመስለኝም። አንዳርጋቸው ጽጌም አማራ ነው - ኅላዌ ዮሴፍ እንዳልሆነው ሁሉ። ስየ አብርሃና ቤተሰቡም አማራ ሆነዋል። ምን ነውር አለበት አማራ መሆን? ማን ያውቃል ገነት ዘውዴም ንስሃ ገብታ ወደፊት አማራ ልትሆን ትችል ይሆናል። መወራረድ እችላለሁ - የኢትዮሚዲያው አብርሃ በላይ ቅልጥ ያለ አማራ ነው። ያ ታዋቂ ጋዜጠኛ ተስፋዬ ገ/አብም በል ሲለው አማራ የመሆን አዝማሚያ ያሳያል - ያቺ መጽሐፍ ተደንቅራበት በጥብጣው ነው እንጂ - የቡርቃ ዝምታ ናት? የተናገሩትና የተፉት ምራቅ አንድ ነው መቼም። ብቻ ይሄም ይሁን - ለበጎ ነው ። ክፉን ካላለፉት ደግ ነገር አይገኝም። ዶክተር ፍስሐጽዮን መንግሥቱ፣ ግደይ ተስፋ ጽዮን፣ ጌታቸው ረዳ፣ ተከስተ ነጋሽ፣ አረጋዊ በርሀ፣ አረጋሽ አዳነ፣ ተወልደ፣ ስንቱን ዶክተርና ፕሮፌሰር አንስቼ እዘልቃለሁ - እነኚህ ሁሉ አማሮች ናቸው፤ ሊያውም አማሮች አማራነታቸው ሰልችቷቸውም ይሁን ካባቸውን ለውጠው ሌላ በሆኑበት ዘመን የአማራን የአንዲት ኢትዮጵያ አስተሳሰብና ዓላማ አንግበው የተነሱ ከአማሮች የበለጡ እውነተኛ አማሮች። ጌታ ይባርካቸው።

ነገሩ እንደተባለው የአስተሳሰብ ጉዳይ ነው አሁንም። እንጂ እንደ አውነቱማ ከሆነ ትግሬ እሚባል ነገር ፈጽሞ የለም። አማራ እሚባል ነገርም እንዲሁ። ኦሮሞ እሚባልማ እንዲያውም በኢትዮጵያ ውስጥ ጠቅላላውን ሠርጹዋል፤ እናም የለም። ሌሎቹም የሉም። ሁሉም ውሸት ነው ፤ እሚያጥበረብር ‹ሚራዥ› አስተኔ የምናብ ፍጡር፣ እማይደርሱበት ሊደርሱበት የተቃረቡ ሲመስልም እሚጠፋ እማይጨበጥ ነገር። የአጭበርባሪዎች ፍልሱም ክስተት። የሰይጣኖች ሥሪት የሆነ የመከፋፈያ ብልሃትና የኢትዮጵያን ጥፋትና ውድመት እሚፈልጉና በ‹ፈንዳቸው› እሚያፈነዱን የታሪካዊ ጠላቶቻችን ልዑክ ነው - ይሄ የዘረኝነት ነቀርሣ የቅርብ ዘመን ትክል ጋንኤል።

እስኪ እውነቱን እንነጋገር። ማን ነው አማራ? አማራ ለመሆን አስቦ፣ ፈቅዶና በውዴታው ተፈራርሞ የተፀነሰ በዚህች ከመመረቋ የተረገመች ሀገር ውስጥም የተወለደ ይኖር ይሆን? ትግሬ ለመሆንስ? እንዲያ ቢሆንማ ከአሜሪካና ከካናዳ እሚወጣ ኢትዮጵያዊ ወይም የሌላ ዓለም ዜጋ በተለይም ከምንዱባኑ የዓለም ክፍል ይኖር ነበርን? ለመሆኑ አማርኛን ለ‹አማራ› ማነው የሰጠው? ኦሮምኛን ለ‹ኦሮሞ› ማን የለገሠው? ትግርኛን ለ‹ትግሬ› ማን አበረከተለት? አንተ ወይም አንቺ እምትናገሪውን ቋንቋ ማን ሰጠህ/ሽ? ወዳችሁ ነው - ‹እኔ እምፈልገው አማርኛን/ሃዲይኛን ነው› ብላችሁ ነው ያገኛችሁት? እንደተወለድህ ከቤተሰብ ተነጥለህ ጫካ ብትጣል ቋንቋ ይኖርህ ነበር? እንዴት ብሎ! እንደ እንስሳቱ በደመ ነፍስ ትጮሃታለህ እንጂ ቋንቋ እሚባል ነገር አይኖርህም ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ እንደተወለድሽ ሌላ ቋንቋ ወደሚነገርበት ቦታ ብትወሰጂ የእናት አባትሽን ቋንቋ ጆሮሽን ቢቆርጡት አትሰሚም። የሰው ልጅ ይህችን ቀላል ተጠየቅ እንኳን አያገናዝብም። ቋንቋ ከተራው ሸሚዝና ከናቴራ ያነሰ ዋጋ ያለው መሆኑን በመዘንጋት ‹የኔ፣ የእኛ፣ የእነሱ› በሚል እየተለያዩ በልሣን ልዩነት ሲራኮት ስናይ ያሳዝናል - ከጥቂት መሠሪዎች ባለፈ ማንም ላይጠቀም። በመንፈሳዊ ዑደት እያደግን ስንሄድ እኮ ከነአካቴው ቋንቋ እሚባል ነገር ካያስፈልገን ይችላል፤ አያስፈልገንምም። አሁን አንዳንዴ በስሜትና

EthioLion.Com

በስድስተኛው ሕዋሳችን ሳንነጋገር መግባባት እንደምንችል ሁሉ የሰው ልጅ የተለዬ ብፅዕና ሲደርስ ቋንቋም ካያስፈልገው እሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ይታመናል፤ አለም። ያ ሩቅ ነው፤ወደ ቅርቡ እንመለስ።

እንዴት ከትግሬነት ፣ ከኦሮሞነት፣ … ወደ አማራነት - ወደሆዳምነት - እዛወራለሁ? የሚል ይኖር ይሆናል። አይፈረድበትም። ምን እናድርግ - አሁን ባለው ሁኔታ ጅል ጅሉን ባሕርያቸውን ትተን ያቺን እምታስወድዳቸውን በአንዲት ሀገር ሥር ሁሉም የመታቀፍ ዓላማቸውን ይዘንላቸው እንደነሱ አማራ እንሁን፤ ግዴላችሁም ይብለጡን፤ እንበለጥ። አለባቸው እምንለውን ችግር በጋራና በመግባባት እናስተካክል። ሀገራችን ጭራሹን ጠፍታ የለየላት ባድማ ከመሆንዋ በፊት ቁጭ ብለን እንመካከርና የረባ ነገር እንሥራ። ለዚህም አማራነትን እንደቅድመ ሁኔታ ብንወስድ እንጠቀማለን እንጂ አንጎዳም። የኛ ማንነት ወዴት ይሄዳል? በአማራነቴ ውስጥ ከምባታነቴን ማን ይነጥቀኛል? በአማራነቴ ውስጥ ትግሬነቴን ማን ይነጥቀኛል? መጥፎው ነገር ዘርን እንደኩይሳ እዚያና እዚህ እያስቀመጡ ‹ኑ በኢትዮጵያዊነታችን እንደራደር› እሚሉት የሞኝ አይሉት የጅል ፈሊጥ ነው። ኢትዮጵያዊነት በድርድር አይገኝም - አንድም በመወለድ አሊያም በመኖርና በመዛመድ። ኢትዮጵያን እያጠፉም ኢትዮጵያዊነት የለም። ለዚህም ነው እነመለስ ኢትዮጵያዊ ሊሆኑ እማይችሉት - ለምን መለስ መቶ ዓመት ቤተ መንግሥት ውስጥ አይኅለትም - ኢትዮጵያዊ ሊሆን ግን ከቶውንም አይቻለውም። አሁን በምሽግ ውስጥ እንጂ በቤተ መንግሥት ያለ ይመስላችኋል? እንዲያ ከሆነማ እስኪ ከኔ ጋር በሱር ማርኬት ወይም መዝናኛ ሥፍራ ይምጣና እንጫወት - ‹ የሀገሬ መሪ አይደለም እንዴ› ? ምን ያስፈራዋል? የምን በሥልክ ማስተዳደር ነው? በአካል ይቅረበን። ‹ዜጎቼ›ና ሌት ከቀን እሚቸነቅልን አይደለንም እንዴ? በዚህ አስተያየቴ ማበድ የምትፈልጉ ‹መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ›። በነገራን ላይ ሂትለር እኮ እንደራሴዎቹን ከስድስት የአውሮጳ ሀገራት በላይ ሥልጣን ላይ በማስቀመጥ ጎረቤቶቹን ለተወሰነ ጊዜ ቀጥቅጦ ገዝቷል። ሲአይ ኤና ኬጂቢም ሞሳድም ይህን ዓይነት ውስጠ ትክል የአገዛዝ ሥልት ይጠቀሙበታል። የኛ ሰው በደማስቆ። የመለስና የኢሳይያስ ታዲያ አዲስ ነገር ነው? እንዴት እንደሚወርዱ አንድዬ ይወቀው እንጂ አሁንማ በደበዘዘው ወርቃማ ዘመናቸው ጫፍ ላይ ነው እሚገኙ። ነገር ሲበዛ ደግ አይደለምና የነገር ድሬን ልጠቀልል ተቃርቤያለሁ።የሰማነውን በልቦናችን ያሳድርልን፤ ሁሉን ማድረግ የማይሳነው እግዚአብሔር ችግራችንን ተመልክቶ ሁላችንንም እንደክፉዎቹና ከርሳሞቹ ሳይሆን እንደደጋጎቹና ለሀገር ተቆርቋሪዎቹ አማሮች በቀናነት ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ግንባታ ቆርጠን የምንነሳ አማሮች ያድርገን። እኔ ባላወቅሁት ሁኔታ የአማራነት ዘውገኝነት አስተሳሰብ እያጎነቆለ ከሆነም እሱን በዋናነት ጨምሮ ከማንኛውም የዘረኝነትና የመድሎ አባዜ ሀገራችንን ፈጣሪ እንዲፈውሳት እንጸልይ። ሆዳምነትና የሥልጣን ጉጉት፣ የሃይማኖት መጥፋትና የፍቅር መቀዝቀዝ፣ የአስተሳሰብ ግልብነትና የዕውቀት ምክነት፣ የወጣት ጨለምተኝነትና ተስፋ መቁረጥ፣ የገንዘብን ጨምሮ ማንኛውም ዓይነት ሱስና መጥፎ ልማድ ከሀገራችን እስከወዲያኛው እንዲወገዱ ፈጣሪ ይርዳን። አሜን። (ያስቀየምኩት ቢኖር ከልብ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤ወድጄ አይደለም)

---

NO, we do NOT agree with everything we post on the site. Some of it is utterly antithetical to our views. YES, we believe it is all worth reading. Know your surroundings; understand the positions of those with whom you disagree. Keep the dialogue and discourse free and open. And let the truth fall where it may.

Source: http://www.rense.com



EthioLion.com